# <u>አማራ መደራጀት ብቻ ሳይሆን ታጥቋልም! – ( አዴሃን )</u>

## የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ (አ.ዴ.ሃ.ን)

አገር ማለት በደስታና በሀዘን እያሳለፍን ከአያት ቅድመ አያት የቆየንን ልጅ ልጆች ተረክበህ የምታስላልፈው የሀብት ሚስጥር ነው፡፡አገር በመሰዋዕትነት እና ጀግንነት ከጠላት ተከላክለህ ለትውልድ የምታስተላልፈው ዋሻ ነው፡፡አገር ማለት እትብትህን ከአፈሩ ሞትህን ከምድሩ ምታጣብቅበት ጌትህ ነው፡፡አገር ግን ያለ ባለቤቱ ባዶ ነው ፤አገር ያለሰው ልጅ ምንም ነው፡፡ ስጋ ያለ አጥንት እንደማይቆም ሁሉ አገርም ያለ ህዝብ አይቆምም፡፡




ኢትዮጵያም ያለ አማራ ኢትዮጵያን ልትሆን አትችልም፡፡ የአማራ መዳከምና መጠንከር ውስጥ የኢትዮጵያን አቋም ማየት ይቻላል፡ አማራ ሲጠነክር ኢትዮጵያም ትጠነክራለች፤ ሲዳከምም ትዳከማለች፡፡ በዘመኗቷው ይህ ስሆነው የኖረው፡፡ አማራ ለአገር ድንበር ጠባቂ ነፃነት አስከባሪ ሆኖ ለዘመናት ኖሯል፡፡ ለዚህም የከፈለውን ዋጋ ይከፈለኝ አላለም፡፡ ለእናት ተሰርቶም አይጠየቅም፡፡ ነገር ግን በምትኩ ያተረፈው ትልቅ ነገር አለ እሱም ከሌላው ኢትዮጵያዊ የላቀ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ነው፡፡ በርግጥ ሌላው ኢትዮጵያዊ ድንበር አላስከበረም ወይም የኢትዮጵያዊነት ስሜት የለውም ማለት አይደለም፡፡ በመልካም እይታ ከታየና ከጥላቻ ነፃ ሆኖ መናገር ከተቻለ ከአያት ቅድመ አያቶቻችንና ከእዛም በፊት ያለን ታሪክ ማስተዋል ከተቻለ ይህን የተቆለለ ሀቅ ለመቀበል አፍታም አይወስድብንም፡፡ አማራ ባለው ልዕለ የአገር ፍቅር ምክንያት ደሙን ስለአገሩ በደስታና በፍቅር አፍስሷል፣ አጥንቱን ስለኢትዮጵያዊነቱ ከስክሷል ፣አገር ኢትዮጵያን ለማቅናት ወጥቷል ወርዷል፡፡ለዚህም ነው በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራው፡፡ አዎ ኢትዮጵያ ለአማራው ህንፃው ናት፡፡ እሱም ለእሷ መሃንዲሷ ነው፡፡ ያድሳታል እንጂ አያፈርሳትም ፤በስስት የሚጠብቃት የአባቶቹ ቃልኪዳን ናት፡፡ ኢትዮጵያ በስልጣኔዋ በዘመኖቿ ነጥቃለች ወድቃለች፡፡ በወርዷ በዘመኖቿ ሰፍታለች ጠባለች ነገር ግን ኢትዮጵያነቷ አልተቀየረችም፡፡ በእነዛ ባለፉ ዘመኖቿ ለሌሎች ጥቁር አፍሪቃዊ ክፍላተ ሀገራት መኩሪያ ፣መነኻሪያ ፣ የነፃነት ተምሳሌት ሆናለች አሁንም ነች፡፡ለነጮችም ቢሆን የስልጣኔ መቅሰሚያ፣ የመለኮታዊ ትምህርት፣ የፍልስፍና ፣ ስነ ፈለግ ፣ የህዝብ አስተዳደር መማሪያ ሆና አስተዋፆዋል ለአለም አበርክታለች፡፡

አሁን ያጣችሁን ካገኘች ጥበብ ከፈጣሪ የተሰጣት የማይነጠቅ ሀብቷ በመሆኑ ወደ ከፍታ ዘመኗ የአሳንሱር ጉዞዋን ትቀጥላለች፡፡ ይህም መሃንዲሳ የሆነ አማራ እንደ ሰው በአገር መኖር ሲችል ሲከበርና የኢትዮጵያዊነት እና የኢትዮጵያ መቀነት መሆኑ ታውቆ ህልውናው ሲጠበቅ ይሆናል፡፡አማራ በደረሰበት ዘሩን መሰረት ያደረገ ጅምላ ጭፍጨፋና የዘር ፍጅት ህልውናውን ለመታደግ በአማራነት ተደራጅቶ ተነስቷል፡፡ ይህን አደረጃጀት አንዳንዶች በዘሩ ላይ የደረሰውን ጥፋት አለመገንዘብ ፣ አማራ በአማራነቱ ከተጀራጀ ሀገር ይፈርሳል በሚል ፍህራት፣ሌሎች ደግሞ በጥላቻና ህብረ ብሔረሰብነት ይጋፉናል በሚል ሲቃወሙት ይታያል፡፡
እውነቱ ግን በአጭሩ አማራ ህልውናውን ለመታደግ በአማራነት መጀራጀት ብቻ ሳይሆን ታጥቋልም፡፡ ይህን አደረጃጀት በመቃወም ወይም በመግፋት ፀረ ወያኔ ነኝ ማለትም አይቻልም፡፡ አገሪቱን ከሮቄ ውስጥ ማውጣት አይቻልም፡፡ ይህችን አገር ከጥፋት የሚያድናት ካለችበት ከዘመነ ግርንቢጥ የሚያወጣት ታዋቂነት ሳይሆን አዋቂ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚጠቅም ፓለቲካ ቢኖር ለመጣው ጨቋኝ ሁሉ መንበርከክ ሳይሆን የመደማመጥ ባህል ማዳበር ነው፡፡ ጭቆና አይለመድም ደግሞም ክብርም አያሰጥም፡፡ራስንም አገርንም ያዋርዳል፡፡ አንድ ትዕልፈታትን ያህል ህዝብ ያላትን አገር ወደ ነበረችበት ልንመልሳት ይገባል፡፡ ድንጋይና ጭቃ ቢቀጣጠሉ ታላቅ ቤት ረጅም አጥር ይሆናሉ፡፡
እኛ ምድራዊያን ሰዎች ለተሰጠችን አጭር ዘመን ብንግባባና ብንረዳዳ ኃይላችን ዛሬ ከፊታችን ላለው ጠላት ብቻ ሳይሆን ለነገ የከፍታ ዘመናችን ድልድይ ይሆነናል፡፡ ህዝባችንን ዝምታና አይቶ ማለፍ ያስጨረሰውን ያህል ለነፃነት ተዋድቆ ያንን ሚያክል ዋጋ አላስከፈለውም ደግሞም አያስከፍለውም፡፡ በዚህ ወቅት የሚጠቅመን ነገር ቢኖር ዛሬ በዛሬ መነፅር እያየን መታገል ምንችል ከሆነ ብቻ ነው፡ ፡ መታገልን ከግል ጀምረን መቀበል ይኖርብናል፡፡ ድል በመቀመጥ አይገኝም፡፡ አቅሙ ኖሮን በዝምታም ሆነ በነቆራ ጊዜን ለማሳለፍ መሞከር የገዳዮችና የጨቋኞች ተባባሪ መሆን ነው፡፡ ታጋዩ የሚሰራውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ፣ ትግል ትልቅ ቦታ ያለውና ክብር የሚሰጥ፣ ሩቅ አሳቢና አስተዋይ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡
መገፋፋትና መጠላለፍ ነፃነትን ያለ ፍሬ ትግልን ያለ አሸናፊ የሚያስቀር እንቅፋት ነው፡፡ ይዘነው የተነሳነውን የትግል መንገድ ጠብቀን የጀመርነውን ግል ያልጨረስነውን ያልተገለጠ የትግል ገፅ አስተውለን እንግለጠው፡፡

ጭቋናን የማይቀበልና የሚታገለው ህዝብ አይሸነፍም፡፡

በቁርጥ ቀን ልጆች አጥንትና ደም ወያኔ ይደመሰሳል!

አማራው ከታወጀበት የዘር ማጥፋትና ማፅዳት እራሱን ይታደጋል!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

ፍፁም አየነው